# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 132 ህዳር 16 ቀን 2003 ገጽ 1


ግዜ
ግንቦት 7 ዜና

**የወቅቱ የግንቦት 7 የትግል ጥሪ**

**“የጋራ ውርደት እንዲያከትም እብሪተኞችን በጋራ እምቢ እንበል፤ ዘረኛውና አዋራጁን የወያኔ ስርዓት ለማስወገድ በጋራ እንነሳ!!!:”**

**ጥርሱን አግጦ ለወጣ የአምባገነኖች የምርጫ ለበጣ ምላሹ “እምቢ ለመብቴ!!!” ብቻ ነው**

## መለስ ዜናዊ በግብጽ ላይ ያስተላለፈው ማስጠንቀቂያ እራሱን እንደ አገር -ወዳድ ዜጋ ለመቅረጽ የሚያደርገው ሙከራ አካል ነው ተባለ

ዘረኛው አምባገነን መለስ ዜናዊ ግብጽ ከኢትዮጵያ ጋር ጦርነት ባታስብ ይሻላታል ሲል በብዙዎች ዘንድ አነጋጋሪ የሆነ ማስጠንቅቂያ መስጠቱ እራሱን እንደ አገር-ወዳድ ኢትዮጵያዊ ለማስቆጠር ከሚያደርጋቸው ሙከራዎች ውስጥ አንዱ ነው ተብሏል።

ዘረኛው አምባገነን ማክሰኞ እለት ለሬውተርስ የዜና አውታር በሰጠው ቃለ መጠይቅ፥ “ኢትዮጵያን ለመውረር የሞከረ ማንኛውም ሃይል ከሞት ተርፎ ታሪኩን ለመናገር ደርሶ አያውቅም። ግብጾችም ከዛ የተለዩ ሊሆኑ አይችሉም፤ ያንንም የሚያውቁ ይመስለኛል፤” ሲል ደስኩሯል። ግብጽ በበኩሏ ይህ የመለስ ንግግር አስገራሚ እና ያልተጠበቀ እንደሆነ በመግለጽ፤ ጦርነት ውስጥ የመግባት ፍላጎት እንደሌላት ገልጻለች።

መለስ ዜናዊ በአንድ በኩል ከግብጽ የኢኮኖሚ እርዳታ እየጠየቀ አብሬሽ ቆማለሁ እንደሚል እና በሌላ ጎን ደግሞ ከተቀሩት የአባይ ተፋሰስ አገራት ጋር ሆኖ ግብጽን በማስፈራራት ሁለቱን ጎን ሲጫወት መቆየቱ ይታወቃል። በተለይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ኢትዮጵያ ውስጥ ድጋፍ ለማግኘት ሲል “የውጭ ጠላት” ዘፈኑን አጠናክሮታል።

የዝግጅት ክፍላችንን ያናገሩ አንድ የፖለቲካ ተንታኝ፤ መለስ ዜናዊ ለግብጽ የሰጠው ማስጠንቀቂያ፣ እራሱን እንደ ኩሩ እና አገር ወዳድ ዜጋ በመቅረጽ፤ ለኢትዮጵያ ያለውን ስር የሰደደ ጥላቻ ለመደበቅ እና ድጋፍ ለማግኘት የሚያደርገው ሙከራ ነው ብለዋል።

## የአማራ ክልል መንግስት ለብአዴን የልደት በዓል 58.6 ሚሊዮን ብር ወጪ አደረገ

ህዳር 11 ቀን፣ ለተከበረው የብሔረ አማራ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ - ብአዴን - የልደት በዓል፣ በአስርት ሚሊዮን ብር የሚቆጠር ገንዘብ ከአማራ ክልል መንግስት ካዝና ወጪ መደረጉን የግንቦት 7 ድምጽ ምንጮች ገለጹ።

በብአዴን ውስጥ ያሉ የዝግጅት ክፍላችን ምንጮች የላኩት ዝርዝር መረጃ እንደሚያሳየው፥ በባህርዳር ከተማ የተከበረው በዓል በሺዎች የሚቆጠሩ እንግዶችን አስተናግዷል። ለተጋባዦቹ መስተንግዶ እና በአሉን ለማሳመር ለተደረጉ ዝግጅቶች ያለፈቃዱ ወጪውን የሸፈነው ደግሞ የአማራ ህዝብ ነው።

ለበአሉ ቅስቀሳ ለሚቀርበው የኪነት ቡድን ወጣት ሴቶችን እና ወንዶችን ለማሰልጠን፤ ለተለያዩ ስብሰባዎች የቀን አበል፤ ለትራንስፖርት፤ በከተማ ኮሪደሮች ለሚገጠጠሙ እና የብአዴንን አርማ ለያዙ ሪቫኖች እና አምፖሎች፤ እንዲሁም ለተጓዳኝ ተግባራት 5 ሚሊዮን ብር፤ በአሉን ለማድመቅ ለተዘጋጁት 240 ተሽከርካሪዎች ነዳጅ ዘይትና ለሾፌሮች አበል 8 ሚሊዮን ብር፤ የከተማዋን እና በአጠቃላይ የክልሉን ጸጥታ ለማስጠበቅ በሚል ሰበብ 16 ሚሊዮን ብር፤ ከተለያዩ ክልሎች እና ከአማራ ክልል ዞኖችና ወረዳዎች የሚመጡ 5000 እንግዶችን ለማስተናገድ 29.6 ሚሊዮን ብር፤ (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## አስረኛው ታላቁ ሩጫ አሁንም የህዝብ ብሶት መግለጫ ሆኖ አለፈ

የህዝብ ድምጽ እንደ ጦር የሚያስፈራው ዘረኛው አምባገነን መለስ ዜናዊ፣ በአስረኛው የታላቁ ሩጫ ዝግጅት ላይ እንዳለፉት አመታት ሁሉ የህዝብ ተቃውሞ ለመስማት መገደዱን የግንቦት 7 ድምጽ ዘጋቢ ከአዲስ አበባ ባስተላለፈው መረጃ አሳውቋል።

የታላቁ ሩጫ አስተባባሪዎች የዘንድሮው ሩጫ መግቢያ ቲኬት ገና ሳይተዋወቅ ተሸጦ አልቋል ብለው ማወጃቸው በብዙዎች ዘንድ አነጋጋሪ ሆኖ መሰንበቱን እና ዝግጅቱ በወያኔ አገዛዝ ቁጥጥር ስር ሳይወድቅ እንዳልቀረ ጥርጣሬ መፍጠሩን መዘገባችን ይታወሳል። በርካቶች አገዛዙ በሩጫው ላይ የሚገለጹትን ተቃውሞዎች ከወዲሁ ለማፈን ሲል ካድሬዎቹ ቲኬቶቹን ለደጋፊዎች እና ለፓርቲ አባላት እንዲያከፋፍሉ በጅምላ ሳይጠቀልለው አልቀረም ሲሉ ግምታቸውን ገልጸው ነበር። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## በጉጂ ዞን በሚኖር አንድ አናሳ ማህበረሰብ ላይ ጥቃት እየተፈጸመ መሆኑ ተዘገበ

በኦሮምያ ክልል በጉጂ ዞን በሚኖሩ የጌዴዮ ብሔረሰብ አባላት እና በንብረታቸው ላይ ጥቃት እየተካሄደ መሆኑን ከኢትዮጵያ የደረሰን ጥቆማ አመለከቷል።

ለግንቦት 7 ድምጽ የዝግጅት ክፍል እና ለሌሎችም መገናኛ ብዙሃን የደረሰው ሪፖርት እንደሚያመለክተው፥ በጉጂ ዞን በአዶላ ረዴ ወረዳ ከሃይለስላሴ ዘመን ጀምሮ የሰፈሩ እና አሁን 767 አባወራዎች የደረሱ የጌዴዎ ብሔረሰብ አባላት ይኖራሉ። በስፍራው ከሰፈሩበት ዘመን አንስቶም በቡና፣ በእንሰት እና በጫት ልማት ስራ ተሰማርተው ሲኖሩ ቆይተዋል። ደርግ የማህበረሰቡን ይዞታ በደን አካባቢነት እንዳካለለ የጠቆመው መረጃ፤ ህዝቡ በወቅቱ ባቀረበው ጥያቄ መሰረት፣ ደኑን ሳይነካ ይዞታውን ግን በነበረበት ሁኔታ እንዲጠቀም ተፈቅዶለታል ብሏል። በዚህ አኳኋንም እስካሁን ድረስ ግብር እየከፈለ በሰላም ሲኖር ቆይቷል።

ይሁን እንጂ፥ ከጥቅምት 1 እስከ 6፣ 2003 አመተ ምህረት ድረስ ባሉት ቀናት ውስጥ የቡና፣ የእንሰት፣ የሙዝ እና የጫት ተክላቸው እንደተጨፈጨፈ እና ለምግብነት በተዘጋጀ ቆጮ ላይም አፈር እንደተጨመረ ለማወቅ ተችሏል።

ለዝግጅት ክፍላችን የደረሰውን መረጃ በመከተል ለማጣራት ባደረግነው ሙከራ፤ ምንም ምክንያት ሳይሰጥ ንብረታቸውን ያወደመው የመንግስት የግብርና ቢሮ እንደሆነ አንድ የአካባቢው ነዋሪ ነግረውናል። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## በኢትዮጵያ ውስጥ የሚፈጸሙ የሰቆቃ ድርጊቶች አሳስበውኛል ሲል የተባበሩት መንግስታት ድርጅት አካል ገለጸ

“ኮሚቴ አጌንስት ቶርቸር” የተባለው እና የተባበሩት መንግስታት ጸረ-ሰቆቃ ስምምነቶች በስራ ላይ መዋላቸውን እንዲከታተል የተመሰረተው አካል፤ በኢትዮጵያ ውስጥ ስለሚፈጸሙ የሰቆቃ ድርጊቶች ስጋቱን ገልጿል።

እንደ ፈረንጆች አቆጣጠር በ1987 በስራ ላይ የዋለው ይህ የተባበሩት መንግስታት የሰብአዊ መብት ስምምነት፤ አገራት በድንበራቸው ውስጥ የሰቆቃ ድርጊት እንዳይፈጸም ጠንካራ እርምጃዎችን እንዲወስዱ እና ከሌላ አገር ሰቆቃን ሸሽቶ የመጣን ሰው ወደመጣበት አገር እንዳይመልሱ ያዛል። ኢትዮጵያውም ከሰባት አመታት በኋላ የስምምነቱ አካል ሆና ነበር።

በስምምነቱ መሰረት የኢትዮጵያ መንግስት ሪፖርት ማቅረብ የነበረበት ሲሆን፤ አስራ አራት አመታት ዘግይቶ በጥቅምት ወር መጨረሻ ላይ መቅረቡን ኮሚቴው ጠቅሷል። ከኢትዮጵያው አገዛዝ ጎን ለጎን የተለያዩ የሰብአዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶች በኢትዮጵያ ላይ ሪፖርት ያቀረቡ ሲሆን፤ ኮሚቴውም የቀረበለትን መረጃ መርምሮ ድምዳሜውን አውጥቷል። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## የቂርቆስ ክፍለከተማ ከ150 በላይ የሚሆኑ ነዋሪዎችን ጠርቶ አካባቢያቸውን በአስቸኳይ እንዲለቁ ትእዛዝ ሰጠ፣ ነዋሪዎቹ በውሳኔው ማዘናቸውን ገልጸዋል

የቂርቆስ ክፍለከተማ ባለስልጣናት በወረዳ 18 ቀበሌ 27 ወይም ሜጋ ህንጻ ፊት ለፊት የሚኖሩ የ157 ቤት ባለቤቶችን ጠርተው ቪላ ቤቶችን አፍርሰው ባለ 4 ፎቅ ህንጻ እንዲሰሩ የማይሰሩ ከሆነ ግን በሁለት ወራት ውስጥ አካባቢውን ለቀው እንዲሄዱ ወይም መንግስት በሚሰጣቸው የኮንዶሚኒየም ቤት ውስጥ እንዲገቡ ትእዛዝ ሰጥቷል።

በመንግስት ድንገተኛ ትእዛዝ የተደናገጡት ነዋሪዎች ለዘመናት የኖሩበትን አካባቢ በሁለት ወራት ውስጥ ልቀቁ ስንባል በእጅጉ አዝነናል ሲሉ ማማረራቸውን ኢሳት የአዲስ አበባ ዘጋቢውን ጠቅሶ ዘግቦአል ።

በአካባቢው የሚገኙት ቤቶች ደረጃቸውን የጠበቁ ሆነው ሳለ አፍርሱ መባሉ አልተዋጠልንም የሚሉት ነዋሪዎች፣ የመንግስት ባለስልጣናት የሚሰሩትን የሚያውቁ አለመስለን ብሎአል ሲሉ ተችተዋል።

በሌላ ዜና ደግሞ የአዲስ አበባ ፍትሕ ቢሮ ከሪል ስቴት ልማት ጋር በተያያዘ ተፈጠረ ላለው ሕገወጥ ተግባር፣ በሕግ መጠየቅ አለባቸው ያላቸውን አልሚዎችና በቀድሞ የአስተዳደሩ ሠራተኞች ላይ ክስ ለመመስረት የሚያስችለውን መረጃ እየሰበሰበ መሆኑን ሪፖርተር የተባለው ለሥር ዓቱ ቅርበት ያለው ጋዜጣ ዘግቧል።

መረጃዎች ተተንትነው ከተጠናቀሩ በኋላ አስተዳደሩ ተጠያቂ ናቸው ያላቸውን አልሚዎችና ሠራተኞች ወደ ፍርድ ቤት እንደሚወስድ ታውቋል። ሕገወጥ ናቸው የተባሉት አልሚዎች ካለፈው (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## ብአዴን እስከመቼ በምርጥ ባርያነት ይፈነጥዛል?

ባርነት ክፉ ነገር ነው። ለጌታ በመስገድ ብዛት በተገኘ ሙገሳ መፈንጠዝ ደግሞ ከባርነትም የባሰ ነው። ባርያ ዛሬ ነፃ ባይሆንም ወደፊት ነፃ የመውጣት ህልም አለው። በጉልበተኛ ፈንጋይ ነፃነቱን ቢያጣም የህሊና ነፃነቱን ያላስደፈረ ባርያ ለሙሉ ነፃነት መታገሉ የማይቀር ነው። የባርያው ከአሳዳሪው ጋር እኩል የመሆን ህልም ትግሉ ሲሰምር እውን ይሆናል። በባርያነቱ እየፈነጠዘ ያለ ባርያ ግን ነፃ ሰው የመሆን ህልሙንም ጭምር አጥቷል። እንዲህ ዓይነቱ ባርያ በአካልም፤ በመንፈስም ባሪያ ነው። ነፃ ሰው የመሆን እድል የለውም።

አፄ ኃይለሥላሴ፣ በመጀሪያዎቹ አስርታት ዘመነ ንግሥናቸው “የባርነት አስወጋጅ ቢሮ” የሚባል ተቋም ነበራቸው። ይህ ቢሮ ገንዘብ ለጌቶቻቸው እየከፈለ በርካታ ባሮችን ነፃ አውጥቷል። በአንፃሩ ደግሞ አንዳንድ “ታማኝ” ባሮች እቢሮው ድረስ እየሄዱ ለጌቶቻቸው ገንዘብ ካስገኙ በኋላ ባርነታቸውን ይቀጥሉ እንደነበር ሰነዶች ያስረዳሉ። ነፃ የሚወጡበትን ገንዘብ ለጌታቸው በመስጠት ተጨማሪ ገቢ አስገኝተዋልና ባሮቹ በጌቶቻቸው ይወደሱ እንደነበር መገመት ይቻላል።

እጅግ በሚያሳዝን ሁኔታ ዛሬ የብሄረ አማራ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ብአዴን) እንደ ድርጅት የሚገኝበት ሁኔታ ይህንን ይመስላል። ብአዴን፣ የህወሃት ምርጥ ባርያ መሆኑ ሳያንሰው በባርነቱ የሚፈነጥዝ ድርጅት ነው። ብአዴን የጌታውን፣ የህወሃትን ማለትም የመለስን ሙገሳን ለማግኘት የሚሆነውን መታዘብ ህሊናን ያቆስላል።

ሰሞኑን የብአዴን ፈንጠዚያ ወቅት ነው። ጌታው ህወሃት - በአምሳለ መለስ ዜናዊ - ባህርዳር ድረስ ሂዶ አሞግሶታል። “ኀበዝና ታማኝ ባርያ” መሆኑ ነግሮታል። ሠላሳ ሻማ ተለኩሶለት ተፍነቅንቋል። “በ1985 ተወልጄ በ2003 እንዴት ሠላሳ ዓመት ሊሞላኝ ቻለ?” ብሎ መጠየቅ አይቻለውም፤ አይገባውምም። ባርያ የሰጡትን ይቀበላል። በ30 ፋንታ 10 ዓመት ነው ቢሉትም ይቀበላል። “የኢህዴን ታሪክ ለኔ ምኔ ነው?” ብሎ አይመራመርም። መጠየቅ እና መመራመር ለባሮች የተሰጠ ነገር አይደለም። አስፈላጊው ነገር ታማኝ ባርነትን እያረጋገጡ ማብላትና መብላት፣ ማጠጣትና መጠጣት፣ ማስጨፈርና መጨፈር እና ማዘረፍና መዝረፍ ነው። የአሳዳሪው መልካም ፈቃድ ከሌለ እነዚህ ሁሉ እንደማይኖሩ ያውቃልና፤ ብአዴን “እድሉን” እየተጠቀመበት ነው።

በዚህ መሃል የአማራ ህዝብ ይታዘባል፤ ይዘግባል። “ተያንዳንዱ ቤት ስንት ስንት ተዋጣ፤ ተመንግሥትስ ካዝና ስንት ወጣ?” እያለ ገበሬው ይጠይቃል። የብአዴንን ጌቶችና አጃቢዎቻቸውን ለመጠበቅ ከትግራይ ለመጡ ዘቦችና ፌርማቶሪዎች 16 ሚሊዮን ብር ወጪ ሆኗል መባሉ፤ ለከተሞች ማሸብረቂያ አምፖሎችና ጨርቆች 5 ሚሊዮን ብር መውጣቱ፤ ለሚበላና ለሚጠጣ 30 ሚሊዮን መመደቡ፤ እንዲያው ለድግስ ብቻ ወደ 60 ሚሊዮን ብር መውጣቱ እብዙ ድሆች አማሮች ጆሮ ደርሷል። ለድግስ የወጣው ገንዘብ የአማራ ክልል ተማሪዎችን በሞላ የዓመት ደብተርና እርሳስ ይሸፍን እንደነበር በየቤቱ ይጉረመረማል። ብአዴንን ግን ይህ አያሳስበውም። ብአዴን ጌታው ያዘዘውን በመፈጸም የሚደሰት ጥርቅም ነው። “አጉርሰኝ” ሲለው ያጎርሳል፤ “ጉረስ” ሲለው በደስታና በችኮላ ይጎርሳል።

የአማራ ህዝብ ብአዴንን የመሰለ አሳፋሪ ድርጅት በታሪኩ ገጥሞት አያውቅም። በባዕድ ወረራ ጊዜ ለጣልያን ያደሩ ባንዶች እንኳን ከዛሬዎቹ ብአዴኖች የተሻለ ክብር ነበራቸው። ከዛሬዎቹም በተሻለ በጌቶቻቸው ጣሊያኖች ይሰሙ ነበር። ብአዴን ግን ራሱን ከባንዳነትም አውርዶ ባርነት ደረጃ ላይ የጣለ ከመሆንም አልፎ በባርነቱ የሚደሰት ድርጅት ነው።

ብአዴንን በተመለከተ ግልጽ ያልሆነ ጉዳይ ቢኖር አንድ ነገር ብቻ ነው። እሱም “እስከ መቼ ነው ጌታው በባርያነቱ እንዲፈነጥዝ የሚፈቅድለት?” የሚለው ጥያቄ ነው። ሁኔታዎች እንደሚያመላክቱት በወያኔ ዓይን የብአዴን ዋጋ እያሽቆለቆለ ነው። ሁሉም የይስሙላ ስልጣን ቢሆኑም አስቀድሞ ከአፈጉባዬነት ቀጥሎ ደግሞ ከመለስ ምክትልነት መባረሩ ብአዴን ለወያኔ የማይጠቅም ያረጀ ባርያ እየሆነ የመምጣቱ ማሳያዎች ናቸው። ከእንግዲህ ወያኔ ይህን አሮጌ ባርያ የሚያሞካሽበት ምክንያት የለውም። የአሁኑ ቡረቃም የስንብት ይመስላል።

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ብአዴንን ከአባላቱ ለይቶ ማየት ይሻል። ከዚህም በተጨማሪ የብአዴንን ከፍተኛ አመራር ከሌላው ለይቶ ይመለከታል። ብአዴን ነፍሳቸውን ሳይቀር ለወያኔ በሸጡ ሰዎች የሚመራ፤ ነፃ የመውጣት ተስፋ የሌለው ራሱ ባርያ የሆነ ድርጅት ነው። አባላቱ ግን ከዚህ የተለዩ ሊሆኑ እንደሚችሉ ግንቦት 7 ያውቃል።

የግንቦት 7 ንቅናቄ ከዚህም በፊትም ደጋግሞ እንደገለጸው፤ በተለያዩ ግዚያት ራሳቸውን ከወያኔ ባርነት ነፃ ለማውጣት በወሰዱት እርምጃ መስዋእትነት የከፈሉ የብአዴን አባላት መኖራቸውን ያውቃል። ግንቦት ለእነዚህ ቆራጦች ትልቅ አክብሮት አለው። ግንቦት 7፣ ሁሉም የብአዴን አባላት ራሳቸውን ነፃ ለማውጣት የግል፣ የወገንና የአገር ግዴታ አለባቸው ብሎ ያምናል።

ዛሬም ጥሪዓችንን እናቀርብላችኋለን። ከወያኔ ባርነት ነፃ ለመውጣት መንገድ መሻት የራሳችሁ ኃላፊነት ነው እንላለን። የገዛ ራሳችሁንና የአማራን ህዝብ እያዋረደ ካለው ብአዴን ተላቀቁ፤ አሊያም እውስጡ ሆናችሁ ድርጅቱን ግደሉት። የብአዴን መኖር ለወያኔ ካልሆነ በስተቀር ለማንም አይበጅም። የወያኔ እድሜ ማጠሩ የማይቀር ነው። ይልቁንስ ወያኔ ያለበሳችሁን የባርነት ካባ እንደለበሳችሁ አዲሱ ቀን እንዳይመጣባችሁ ዛሬውኑ የነፃነት ትግሉን ተቀላቀሉ እንላለን።

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!**

### ወያኔ የአገሪቱን ለም መሬት ለባዕዳን እየሸጠ በምግብ እራሳችንን እንችላለን የሚለው ዕቅዱ ፋይዳ ቢስ መሆኑን የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አካል የሆነው ዩ ኤን ሀብታት ገለጸ

ኢትዮጵያ ሰፋፊ የእርሻ መሬቶችን ለውጭ አገር ባለሀብቶች በመስጠት የወደፊቱን ህዝብ ለመቀለብ ያስችለኛል ብላ ብታስብም እንኳንስ የወደፊቱን ቀርቶ አሁን ያለውንም ህዝብ መመገብ አትችልም ሲል የተባበሩት መንግስታት ድርጅት አካል የሆነው ዩኤን ሀቢታት ገለጸ፣ ፣

ድርጅቱ "የአፍሪካ ከተሞች ሁኔታ በ2010" በሚል ርእስ ባወጣው ሪፖርት ከ80 በመቶ በላይ የሚሆነው የአዲስ አበባ ህዝብ እንደ ቤንጉዌላ፣ ሞቃዲሾና ፍሪታውን ህዝብ እጅግ አስከፊ በሆነ የኑሮ ደረጃ ውስጥ የሚገኝ ነው።

በኢትዮጵያ እና በሌሎች የአፍሪካ አገሮች የእርሻ መሬት ለውጭ ባለሀብቶች በስፋት እየተሰጠ ቢሆንም የከተሞችን እና የምግብ ችግርን በመቅረፍ በኩል ያለው ሚና አነስተኛ ነው ሲል ሪፖርቱ ገልጿል።

ቻይና ባለፈው አመት ከ1 ሚሊዮን በላይ ዜጎቿን ወደ አፍሪካ በመላክ ያመረተችውን ምርት ወደ አገሯ ሰዳለች የሚለው የተመድ ሪፖርት፣ ይህ አይነቱ "ቻይናውያንን ወደ አፍሪካ መላክና የእርሻ ምርቶችን ወደ ውጭ የመላክ አካሄድ" በከተሞች የሚታየውን የስራ አጥነት ችግርና የምግብ እጥረት ሊቀርፍ ቀርቶ በህብረተሰቡ ውስጥ ያለውን ችግር ይበልጥ የሚያባብስ ነው ።

ኢትዮጵያ በአለፈው አመት 150 ሺ ቶን ስንዴ ወደ አገሩዋ ማስገባቷን፣ በ2008 ደግሞ ከ11 ሚሊዮን ህዝብ በላይ መራቡን ያስታወሰው ሪፖርት፣ የኢትዮጵያ መንግስት ሰፋፊ የእርሻ ቦታዎችን ለውጭ ባለሀብቶች በመስጠት የወደፊቱን ህዝብ መመገብ ቀርቶ አሁን ያለውንም ህዝብ መመገብ አልቻለም ብሎአል።

በኢትዮጵያና በአንዳንድ ያፍሪካ አገሮች የሚታየው የእርሻ መሬት ሽያጭ ግልጽነት የጎደለውና ለምዝበራ የተጋለጠ በመሆኑ አንዳንዶች አግሮ ኢምፔሪያሊዝም እያሉ ይጠሩታል ሲል ሪፖርቱ አመልክቷል፣ ፣ ተመድ ሀቢታት በአፍሪካ ውስጥ የሚታየውን የመሬት ሽያጭ አጥብቆ እንደሚቃወም ይታወቃል።

### የቂርቆስ ክፍለከተማ ከ150 በላይ የሚሆኑ ነዋሪዎችን . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ወር ጀምሮ ዕርምጃ እየተወሰደባቸው የሚገኝ ሲሆን፣ ወደ ፍርድ ቤት የሚሄዱት በአስተዳደሩ የከፋ ‹‹ወንጀል›› ፈጽመዋል የሚባሉት እንደሆኑ ጋዜጣው ዘግቧል።

አንዳንድ አልሚዎች በሊዝ ቦርድ ከተወሰነላቸው በተጨማሪ ከመሬት ባለሥልጣን ሠራተኞች ጋር በመመሳጠር የማይገባቸውን ቦታ ወስደው ግንባታ ማካሄዳቸውን፣ በዚህም መንግሥት ማግኘት የነበረበትን ገቢ እንዲያጣ አድርገዋል ያላቸውን አልሚዎች፣ በሕገ መንግሥቱ መሬት አይሸጥም አይለወጥም ተብሎ ቢደነገግም፣ ግንባታ ሳያካሂዱ መሬት በመሸጥ የማይገባቸውን ጥቅም በማግኘታቸው አስተዳደሩ በሕግ ከመጠየቅ ወደኋላ እንደማይል ተመልክቷል።

ስተዳደሩ ከዚህ በተጨማሪም ለሪል ስቴት ልማት በወሰዱት ቦታ ላይ የፕሮግራም ለውጥ ባደረጉ፣ የአገልግሎት ለውጥ ባደረጉ፣ በሕገወጥ መንገድ አስፋፍተው በያዙት ቦታ ላይ ግንባታ ባካሄዱ፣ የተሰጣቸውን ቦታ ለሦስተኛ ወገን ባስተላለፉ፣ ያለግንባታ ፈቃድ የገነቡ አልሚዎች በሙሉ ጥፋተኛ ናቸው የሚል ድምዳሜ ላይ ደርሷል፡፡

እነዚህ አልሚዎች ባጠፉት ጥፋት መሠረት የአካባቢውን ከፍተኛ የሊዝ ጨረታ ዋጋ እንዲከፍሉ አስተዳደሩ ወስኗል፡፡ በአሁኑ ወቅት ግብረ ኃይሉ ጥፋተኛ ያላቸውን አልሚዎች ያሉበትን አካባቢ ከፍተኛ የሊዝ ጨረታ ዋጋን በማጥናት ላይ መሆኑን ከጋዜጣው ዘገባ ለመረዳት ይቻላል።

ክፍያውን ለመክፈል ፈቃደኛ የማይሆኑ አልሚዎችን ካርታቸውን እንደሚያመክን፣ በሕግ እንደሚጠይጠቃቸውና ያለፈቃድ የተገነባውንም ግንባታ እንደሚያፈርስ ግብረ ኃይሉ ወስኗል፡፡

በከተማው አስተዳደር በ141 አካባቢዎች 125 አልሚዎች ስድስት ማሊዮን ካሬ ሜትር ቦታ ለሪል ስቴት አልሚዎች የተሰጠ ሲሆን አብዛኛዎቹ የሪል ስቴት አልሚዎች በሕገወጥ ተግባር ላይ ተሰማርተዋል ።

አልሚዎቹ የአስተዳደሩ ዕርምጃ ግብታዊ ነው፤ ሕግን የተከተለ አይደለም በሚል መቃወማቸውን ቢቀጥሉም፣ በአስካሁኑ ሒደት ተቃውሞቻቸው ተሰሚነት እንዳጣ መረዳት ችለናል ሲል ጋዜጣው ገልጿል።

(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

በግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ የህዝብ ግንኙነትና ቅስቀሳ ዘርፍ በሳምንት አንዴ የሚዘጋጅ ድርጅታዊ ልሳን

የፖስታሳጥን ቁጥር ፡- POBox: 4916
2003EX Haarlem, The Netherlands

## ያለፈው ወር የመለስ የሹመት እስክስታ የማይሸፍነው የትግራይ ገዥ ጉጅሌ ፍጹማዊ ዘረኛ አማባገነናዊነትና ዘራፊነት

### የግንቦት 7 የኢትዮጵያን ወቅታዊ ሁኔታ ትንታኔ

ሰሞኑን መለስ ዜናዊ አዳዲስ ሚኒስትሮችንና አምባሳደሮችን መሾሙን ነግሮናል። በዚህ ጽሁፍ የምናተኩረው ሹመቱ ላይ አይደለም። ትኩረታችን በዚህ ሹመት አማካይነት ዘረኛው አምባገነን መለስ ዜናዊ ሊያስተላልፍልን በፈለገው መልእክት ላይ ነው።

መልእክቶቹ ግልጽ ናቸው። የተሾሙትን ግለሰቦች የዘር ጀርባ ተመልክተን "ሹመቱ ምንም አይነት የትግራይ ዘረኛነት የለበትም "እንድንል ነው።

መለስ ዜናዊና ዘረኛ ስርአቱን የሚደግፉ ጀሌዎቹ ሊነግሩን የሚፈልጉት" ትግራዋዩ ስዩም መስፍን ከውጭ ጉዳይ ተነስቶ በቦታው የደቡቡ ሃይለማሪያም ደሳለኝ መተካቱና በሌሎችም የሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች በርካታ የደቡብ ሰዎች መመደባቸው ስርአቱ ዘረኛ አለመሆኑን የሚያሳይ ነው "የሚል መልእክታቸውን ነው።

ወያኔዎች ይህን መልእክታቸውን ልብ እንድንል በየሚድያው ካቀረቡት የሰሞኑ የሚንስቴሮችና ቀጥሎም የአምባሳደሮች የሹመት የስም ዝርዝር ጋር ትኩረታችንን ለመሳብ በማሰብ አንድ የፕሮፓጋንዳ ነጥብ ሲያሰተጋቡ ነበር። በአገዛዙ ስር ባሉ ጋዜጦችና ድረ-ገጾች ላይ ከተሿሚዎች የስም ዝርዝር ጋር ሽንጥ ተደርጋ የወጣች መሰሪ ፕሮፓጋንዳ እንደሚከተለው ትነበባለች።

"ከዚህ በላይ ስማቸው የተዘረዘሩትን ሚኒስቴሮች ወይም አምባሳደሮች ለመሾም የተወሰደው መመዘኛ ችሎታና ችሎታ ብቻ ነው "ትላለች።

የመልእክቱ አላማ ግልጽ ነው። ሰዎቹን ስንሾም ዘረኛነትን፣ በሌላ ቋንቋ ትግሬነትን፣ መስፈርት አላደረግንም ለማለት ነው። ወያኔ በዘረኛነቱ ከሃገሬው አልፎ በውጭ መንግስታትም እየታወቀ መምጣቱ ትንሽ ያሳሰበው ለመሆኑ ፍንጭ ነበሩና መልእክቱ ለሃገሬውም ብቻ ሳይሆን ለመጽዋቾቹ ፈረንጆችም ጭምር እንደሆነ ግልጽ ነው።

"የፖለቲካ ታማኝነትን መስፈርት አላደረግንም "የሚል መልእክት ለማስተላለፍ ተፈልጎ የተጻፈ ነው ብለን እንዳንተረጉመው ተሿሚዎቹ በሙሉ የጌቶቹ ፓርቲ –ህዝባዊ ወያኔ ሃርነት ትግራይ - ጠፍጥፎ የሰራቸው፣ ሎሌ ድርጅቶች ታማኝ ካድሬዎች ናቸው። በስም ዝርዝሩ ውስጥ የመለስ መጋለቢያ ጌኛ ካድሬ ሳይሆን በችሎታው ብቻ የተሾመ ሰው የለም። በመሆኑም መልእክቱ ዘረኛነትና ሹመት የተለያዩ መሆናቸውን ለማሳመን የሚጥር እንደሆነ ግልጽ ነው።

እየተነገረን ያለው" ሰዎች የተሾሙት በፖለቲካ ታማኝነታቸው አይደለም " የሚለውን ቢክዱትም ሊካድ የማይችል ሃቅ ለመሸፈን አልነበረም ::መልእክቱ "ትግሬነትን ለከፍተኛ ሹመት የሚያበቃ መስፈርት ማድረግ አቁመናል" የሚል ነው። ይህ በራሱ መልእክቱን አስገራሚ ያደርገዋል። አንዱ የመልእክቱ አላማም፣ ዋንኛው ባይሆንም፣" ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርን የሚያክል ቁልፍ መስሪያ ቤት ሳይቀር የትግራይ ተወላጅ ባልሆነ ሰው እንዲያዝ አድርገናል " ነው።

እኛ እዚህ ላይ ሃይለማሪያም ደሳለኝ ከደቡብ ይምጣ እንጅ በመንፈሱም ሆነ በድርጊቱ ከትግራይ ጌቶቹ የበለጠ ትግራዋይ ነው ማለት አያቅተንም። ይህ እንግዳ ነገር አይደለም። በሃገራችን ከጣልያንም በላይ ጣልያን የሆነ፣" እኔ የሃያሉ አሽከር" በማለት በጣልያን ስም የሚምል ባንዳ ነበር። የኦሮሞን እና የአማራን ህዝብ፤ እንዲሁም የደቡብና ሌሎችንም ህዝቦች ለዘመኑ የትግራይ ገዥዎች በባርነት እያስረገጡ ሆዳቸውን የሚሞሉ፤ በወያኔ ጌቶቻቸው ስም የሚምሉ በርካታ ከሃዲዎች ባሉበት ሃገር ደሳለኝ ደሙ ደቡብ ልቡ ትግራዋይ ነው ብንል ማጋነን አይሆንም። ይህን አባባል የሰነዘርነውም ያለ በቂ ማስረጃ አይደለም።

ከጥቂት ወራት በፊት የመተካካቱን ጉዳይ አንስተው መለስና በጣት የሚቆጠሩ ዘረኛ ሴረኞቹ በረከት ሰምኦንንና የደህንነቱን ሃላፊ ጌታቸው አሰፋን ጨምሮ ስብሰባ አድርገው ነበር። የመተካካቱ ጨዋታ የትግራዩን ገዢ ጉጅሌ የስልጣን የበላይነት በማይነካ መልኩ እንዲከናወን እነማንን መሾም እንደሚገባ ለመመካከር የተደረገ ስብሰባ እንደነበር የግንቦት 7 ንቅናቄ ከብአዴኖች አካባቢ መረጃ ደርሶት ነበር። ከደቡቡ ሃይለማሪያምና ከሌሎችም የሚኒስትርነትና የአምባሳደርነት ሹመት ጀርባ ያለው ሃቅ ይህ ነው። በወያኔ ምርጦች ስብሰባ ላይ የአንድ ሰው ስም ለሹመት እንዲታጭ ሲቀርብ መለስ ዜናዊና የቅርብ ባለደረቦቹ በተደጋጋሚ:-

"ሰውየው ጸረ-ትግሬ አለመሆኑን በደንብ ታውቃላችሁ ወይ "?የሚል ጥያቄ ያነሱ እንደነበርና የደህንነቱ ሃላፊ ጌታቸው አሰፋ በሚጠቆሙት ግለሰቦች ላይ ያለውን መረጃ እያቀረበ የተሿሚዎቹ ምርጫ እንደተከናወነ ሰምተናል። በረከት ስምኦን አንዱ እርሱ ለሹመት ያቀረበው የብአዴን አባል የሆነ የጎንደር ተወላጅ ጸረ ትግሬ ነው በሚል ፍረጃ ወያኔዎቹ ያልተቀበሉት በመሆኑ ቅር ተሰኝቶ፣ ስለስብሰባው ሂደት ለብአዴን ጓደኞቹ የተናገራቸው ቃላት መለስና በዙሪያው የሰበሰባቸው ዘረኛ የትግራይ ተወላጆች የገዛ ጥላቸውን ከማያምኑበት ደረጃ ላይ መድረሳቸውን የሚያመላክት ነው።

"ሰዎቹ ሳርና ቅጠሉ ሳይቀር ጸረ ትግሬ ይመስላቸው ጀምሯል "ነበር በረከት ስምኦን ያለው ::እነመለስ አንድ ሰው ከመሾማቸው በፊት ጸረ-ትግሬ ላለመሆኑ መረጃ ስጡን ብለው ሲወተውቱ የከረሙት ተሿሚው ሰው በአይኑ አይቶት የማያውቀውን ደሃ የትግራይ ገበሬ ይጠላል ወይ የሚል ስጋት ስላደረባቸው እንዳልሆነ ግልጽ ነው። ጥያቄው ይሰነዘር የነበረው ሊሾም እየታጨ የነበረው ሰው፣ የትግራይ ገዢ ጉጀሌ በጁ ባግበሰበሰው የሃገር ሃብትና ስልጣን ላይ ቅሬታ ያደረበት፣ ስለ መለስና በዙሪያው ስላሰባሰባቸው ሰዎች ሲያስብ አይኑ የሚቀላ ነወይ ለማለት ነበር። እንግዲህ በዚህ መመዘኛ አልፈው የመጡ ሰዎችን ነበር "በችሎታቸው ከዘር መድሎ ውጭ መደብናቸው "የተባልነው።

ይህም አልበቃ ብሎ ለነሃይለማሪያም ደሳለኝ ሞግዚት እንዲሆን የዘረኛው ስርአት አገልጋይና የመለስ ዜናዊ የቅርብ ወዳጅ የሆነው ብርሃነ ገብረክርስቶስ በውጭ ጉዳይ ሚንስቴር መስሪያ ቤት ውስጥ በሚኒስቴር ዴኤታነት መመደቡ ተነግሮናል። ሚኒስትሩ ብርሃነ ወይስ ሃይለማሪያም ለሚለው ጥያቄ መልሱ ግልጽ ነው። ብርሃነ ነው ለስራ ጉዳይ ወደ ሚኒስቴር ደሳለኝ ቢሮ የሚሄደው ወይንስ ሚኒስትሩ ሃይለማሪያም ወደ ሚኒስቴር ዴኤታው ወደ ብርሃነ ቢሮ የበታቹን ሊያናግር ይሄዳል ?የዚህም ጥያቄ ምላሽ ግልጽ ነው።

ከወያኔ አሰራር እንደምናውቀው የስልጣን የበላይነት የችሎታና የሹመት የበላይነት ውጤት ሳይሆን የዘር ትስስር ነው። ትንሿ የወያኔ ካድሬ ትልቁን የኦህዴድንና የብአዴንን ካድሬ ስታዝና ስታንቀጠቅጥ እንደኖረች እናውቃለን። አንድ የትግራይ ሃምሳ አለቃ አንድን ከትግራይ ዘር ያልመጣን ጄነራል እንደሚያሽቆጠቁጥ ግልጽ ነው። ሰለዚህ ዛሬ በየመስሪያ ቤቱና በኤምባሲው ከተመደቡት የሌላ ዘር ጭምብል ካጠለቁ ሰዎች ጀርባ በየሚስኒቴር መስሪያ ቤቱም ሆነ በየኤምባሲው ፈላጭ ቆራጮቹ ከመለስ ምርጥ ዘር የተመረጡ በተለያዩ ክፍሎች የተመደቡ በአደባባይ የሚንስተርና የአምባሳደርነት ሹመት ያልተሰጣቸው የትግራይ ሚኒስቴሮችና አምባሳደሮች ናቸው።

ስለሰሞኑ ሹመት ሌላም ሌላም ማለት ይቻላል።

መለስ ዜናዊ ለምን አብዛኛዎቹን ተሿሚዎች ከደቡብ አደረገ ?ለምን የመለስ ውቃቢ ከበኩር ተለጣፊዎቹ፣ ከብአዴንና ከኦህዴድ ላይ ተነሳ ?ለምንስ ወደ አዲሶቹ የደቡብና የሌሎች አናሳ ብሄረሰቦች ተለጣፊ ድርጅቶች ሄደ ?የመለስን ዘረኛ የከፋፍለህ ግዛ ፖሊሲ በማንተራሰ ለነዚህ ጠያቄዎች በቂ ምላሽ መስጠት ይቻላል። ይሁንና ከሰሞኑ ሹመት ጋር የተያያዘው ቁም ነገር ይህ ሰላልሆነ እንዘለዋለን። ዋናው የሹመቱ ቁም ነገር መለስና በስልጣንና በነዋይ ሱስ የደነዘዙ ዘረኛ ማህበርተኞቹ የኢትዮጵያን ህዝብ አይንህን ጨፍንና እናሞኝህ የሚል የንቀት መልእክት ያስተላለፉበት መሆኑ ነው።

የሰሞኑ የወያኔ ሹመት ሰዎችን በችሎታቸው ነው የመደብነው የሚል መግለጫ ተለጥፎበት የወጣው ስለአዲሶቹ ተሿሚዎች ተብሎ አይደለም። የነባር ተሿሚዎችንና አዳዲስ የትግራይ ተወላጆችን ሹመት ለማሳመር ነው።

ቅድም እንደገለጽነው ዘረኛው መለስ" ሰዎቹን በሃላፊነት ላይ ያስቀመጥኩት በችሎታቸው ነው "እያለን ነው። ይህ ማለት" መከላከያው፣ ደህንነቱ፣ ቁልፍ የሆኑ የኢኮኖሚ አውታሮች በትግራይ ተወላጆች እጅ ተይዘው እንዲቀጥሉ የምናደረገው እነዚህ ሰዎች በዘራቸው ትግራዋይ ስለሆኑ ሳይሆን በችሎታቸው የላቁ ስለሆኑ ነው "ለማለት ነው።

በጠቅላይ ሚኒስትሩ ቢሮ ውሰጥ ቁልፍ በሆኑ የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊና የደህነነት ጉዳዮች ላይ ዘረኛውን መለስ ዜናዊን የሚያማክሩት በሙሉ የትግራይ ተወላጆች ናቸው። በመሆናቸውም የሃገሪቱ የፌደራል ቋንቋ የሆነውን አማርኛ ቋንቋ ሳይጠቀሙ በሃገር ጉዳይ ላይ መክረው ውሳኔ **(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)**

## ያለፈው ወር የመለስ የሹመት እስክስታ . . . (ከገጽ 3 የዞረ)

በመሃላቸው ትግርኛ የማይናገር ሰው የለምና። ይህ የሚያሳየው ወሳኝ የሆነው የሀገሪቱ ስልጣን እንዴት ዘረኛ በሆነ መንገድ የተሰባሰበ መሆኑን ነው። በመከላከያ ሚኒስቴር ውስጥ የመከላከያ ሰራዊቱ አዛዥ ሳሞራ የኑስና የሰራዊቱን ከፍተኛ ስልጣን የያዙት 7 ከፍተኛ የጄነራልነት ማእረግ ያላቸው ባልደረቦቹ የሚያደርጉት ስብሰባ የሀገሪቱን ፌደራል ቋንቋ መጠቀም አያስፈልገውም። ወያኔ ስልጣን ላይ ከወጣ ከሃያ አመት በኋላም በትግርኛ ብቻ ተነጋግረው የሚያበቃበት ሁኔታ ዛሬም እነደቀጠለ ነው። እንዲሁ በተመሳሳይ ከአርባ በላይ የሚሆኑ የሀገሪቱ ከፍተኛ ጀነራሎች በሃገር መከላከያ ጉዳይ ላይ ውይይት ለማድረግ የሀገሪቱን የስራ ቋንቋ አማርኛን መጠቀም አያስፈልጋቸውም። ጉዳያቸውን በትግርኛ ጀምረው በትግርኛ መጨረስ የሚችሉበት ሁኔታ የሚያሳየው ዘረኛነት የሰራዊቱ የከፍተኛ ስልጣን መያዢያ መስፈረት ሆኖ መቀጠሉን ነው። በደህንነት ጉዳይም መስሪያ ቤቱን በሙሉ እንዳሻቸው ከሚያዙት የትግራይ ተወላጆች በተጨማሪ አዲሱን የጠቅላይ ሚኒስትሩን የደህንነት ጉዳይ አማካሪ፣ የቀደሞውን የትግራይ ክልል ፕሬዚደንት አለቃ ጸጋዬን ጨምሮ በሙሉ የተያዘው በትግራይ ተወላጆች ነው።

ከዚህም በተጨማሪ የወያኔ ዘረኞች ከፍተኛ ጥቅም የሚገኝባቸውን ማናቸውም ሃብት የሚያፈሩ ተቋማት ውስጥ ቁልፍ የሆኑ ቦታዎች እንደያዙና ዘረኛ በሆነ መንገድ በመጠቃቀም ከፍተኛ ሃብት እየዘረፉ ያለበት እውነታ አልተቀየረም። ይህ አልበቃ ብሎ በሚቀጥሉት አመታት ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ያስገኛሉ ተብሎ የታሰቡትን የመብራት ሃይልና የስኳር ኮርፖሬሽን መስሪያ ቤቶች በቀንደኛው ዘረኛ በመለስ ዜናዊ እጅ ተጠቃለው እንዲገቡ መወሰኑ ከአዲሱ ሹመት ጋር የቀረበ ዜና ነበር። ይህ የሚፈጸመው በአገዛዝ ስርአቱ ውስጥ የትግራይ ምርጦች የያዙትን የኢኮኖሚ የበላይነት ለማስረገጥ ሆን ተብሎ እንደሆነ መታወቅ ይኖርበታል።

መለስ ዜናዊ አባይ ጸሃዬን ከሚኒስትርነት አንስቶ የስኳረ ኮርፖሬሽን ሃላፊ ሲያደርገው አባይን እያዋረደ ሳይሆን ራሱን ጠቅሞ አባይ ጸሃየንም ለመጥቀም ነው። የዘረኞቹን የበላይነት እያስጠበቀ ነው። ስኳር በሚቀጥሉት ጥቂት አመታት እስከ 500ሚሊዮን ዶላር የውጭ ምንዛሪ የሚያስገኝ የንግድ ዘርፍ እንደሚሆን በሚተነበይበት ወቅት የትግራይ ተወላጅ ያልሆነን ሰው በዛ ቦታ ላይ መመደብ ለመለስ ዜናዊና ለዘረኛ አጋሮቹ የማይታሰብ ነው። የውጭ ጉዳይና የተቀሩትንም ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች በሙሉ ለደቡቦች አስረክቦ መለስ ዜናዊ የጦር ሃይሉን፣ ደህንነቱንና ወሳኝ የሆኑትን የሃገሪቱን የሃብት ምንጭ ተቋማት በዘር ልጅነታቸው በመለመላቸው የትግራይ ተወላጆች ይዞ እስከቀጠለ ድረስ የዘረኛው የትግራይ ገዥ ጉጅሌ የፈላጭ ቆራጭነትና የዘራፊነት ጀንበር እንደማይጠልቅ ያውቃል።

መለስ ዜናዊና የትግራዩ ገዢ ጉጅሌ በተጠናወታቸው የህዝብ ንቀት በሽታ የተነሳ ያልገባቸው የኢትዮጵያ ህዝብ ጉልበትና ሃብት የስልጣን ምንጭ እንደሆነ ጠንቅቆ የሚያውቅ መሆኑን ነው። ዛሬም መለስ ዜናዊ በሃገሪቱ ውስጥ ያለውን ወሳኝ የሃብት ምንጭ ከትግራይ ዘር ባሰባሰባቸው ምርጦች እጅ እንደተቆጣጠረ ነው። መለስ ዜናዊ ህዝብን ሲሻው ሊያሳድድ፣ ሊያስርና ሊገድል የሚችል ሰራዊቱንና ደህንነቱን በሙሉ በዘር ባደራጃቸው የትግራይ ተወላጆች እጅ እንዳስያዘ ነው። ይህን ሰራዊት መለስ" ጃስ "ቢለው በአንድ ቀን ማታ ሃይለማሪያም ደሳለኝንና የተለጣፊ ድርጅቶችን መሪዎች ቁርጥምጥም አድርጓቸው እንደሚያድር ይታወቃል።

እንዳውም የቅርብ ጊዜው ሹመት የሚያሳየው የዘረኛነትን መላላት ሳይሆን በተቃራኒው መለስ ዜናዊ ሃብትንና ጉልበትን የበለጠ በትግራይ ተወላጅነታቸው በተመረጡ ባለሟሎቹ እያስያዘ እንደሆነ ነው። መለስ ዜናዊ በትራንስፎርሜሽንና በመተካካት ፖለቲካ ስም ሽህ ግዜ ሲያስካካ፣ ሽህ ሃይለማሪያም ደሳለኞችን ለላንቲካ ቢደረድር የስርአቱ ዘረኛነት ከግለሰቦች መቀያየር ተሻግሮ ተቋማዊ ሆኗልና የሚቀየር ነገር አይኖርም"::

የዘረኛነት ዛር ከመለስ ዜናዊና ከሚመራው ጉጅሌ ይወጣል "ማለት" ዉሃ ሽቅብ ሊፈስ ይችላል" ከሚል ከንቱ አባባል ልዩነት አይኖረውም። ዘረኛነት የሚያከትመው በወያኔ መቃብር ላይ ብቻ እንደሆነ ሃገሬው ከተረዳው ሰነበተ። የሰሞኑ ሹመት "ከሃፍረተ -ቢስ የዘረኞች ብልጣብልጥነት የተለየ ትርጉም የለውም "የምነለው ለዚህ ነው።

## በጉጂ ዞን በሚኖር አንድ አናሳ ማህበረሰብ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ተጎጂዎቹ ጥቃቱ እንደተፈጸመባቸው ለአዶላ ረዴ ወረዳ አስተዳደር አቤቱታ ለማቅረብ በብዛት ጉዞ ቢጀምሩም፤ የፌዴራል አድማ በታኝ ፖሊስ ከስፍራው ደርሶ እንዳስቆማቸው እና በአስለቃሽ ጭስና በጥይት የታጀበ ከፍተኛ ድብደባ ፈጽሟል። በርካታ ንጹሃን ቆስለዋል፤ ዘጠኝ ዜጎችም ታስረዋል። ሪፖርቱ፥ ችግሩ በተከሰተበት ስፍራ የማይኖሩ እና በወቅቱም በስፍራው ያልነበሩ ሰዎች የጌዴኦ ብሔረሰብ አባላት በመሆናቸው ብቻ መታሰራቸውን ገልጾ፤ ሁኔታውን በጌዴኦ ማህበረሰብ ላይ ያነጣጠረ "ዘረኛ ጥቃት" ብሎታል።

የግንቦት 7 ድምጽ ጥቆማውን ተከትሎ ወደ አካባቢው ስልክ በመወደወል ጥቃቱ መፈጸሙን ያረጋገጠ ሲሆን፤ ህዝቡ እስካሁን መፍትሄ እንደተነፈገም ለማወቅ ተችሏል።

በጉጂ ዞን ከዚህ ቀደም ከአላሙዲ የወርቅ ማእድን ጣቢያዎች ጋር በተያያዘ ተቃውሞ ተነስቶ እንደነበር መዘገባችን ይታወሳል።

## የአማራ ክልል መንግስት ለብአዴን . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

በድምሩ 58.6 ሚሊዮን ብር ከአማራ ክልል ካዝና ወጪ መደረጉን ምንጮቻችን ገልጸዋል። የህዝብ ገንዘብ ለፓርቲ ጉዳይ መዋሉ ህገ-ወጥ ከመሆኑ በተጨማሪ፣ ዝግጅቱ ይህንን ያህል ገንዘብ እንደማይፈጅ እና አገዛዙ ለዘረፋ እንዲመቸው የፈጠረው ስልት እንደሆነም ጠቅሰዋል።

ለዝግጅት ክፍላችን የደረሰው መረጃ እንደሚያሳየው፥ በበአሉ ሰሞን ጸጥታ ለማስከበር የክልሉ ፖሊስ፣ ሲቪል ደህንነት፣ መከላከያና ልዩ ሃይል አልበቃ ብሎ፤ የፌዴራል ፖሊስ ከአዲስ አበባ መጥቶ በባህርዳር እንዲሰማራ ተደርጓል። ከትግራይ ክልል የመጡ ወጣት ሰላዮችም በከተማዋ ማእዘናት ሁሉ ተሰማርተው ጥበቃ እንዳደረጉ ለማወቅ ተችሏል። እነዚህ ወጣቶች ከዚህ ቀደም ዘረኛው አገዛዝ ልዩ ስልጠና ሰጥቶ በወረዳ አማካሪነት ሽፋን በአገሪቱ ዙሪያ የመደባቸው እንጂ ለበአሉ ሲባል አዲስ የመጡ እንዳልሆኑ መረጃው ገልጿል።

ብሔረ አማራ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ የአማራን ህዝብ እወክላለሁ ይበል እንጂ፤ በክልሉ ህዝብ ከመጠላቱ በተጨማሪ፣ የአማራ ብሔር አባላት ባልሆኑ ግለሰቦች መመራቱ በድርጅቱ የዝቅተኛ ደረጃ አባላት ዘንድ የረዥም ጊዜ የምሬት ምንጭ ሆኖ መቆየቱ ይታወቃል።

## አስረኛው ታላቁ ሩጫ አሁንም . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

በተጨማሪም፥ የሩጫው መስመር በቤተመንግስቱ እና በሌሎች የመንግስት ተቋማት ህንጻዎች በኩል እንዳያልፍ ለውጥ እንደተደረገበት ይታወቃል።

ይሁን እንጂ፥ እሁድ እለት በተካሄደው ዝግጅት ላይ በርካታ ወጣቶች ብሶታቸውን ሲገልጹ ቆይተዋል። በሩጫው ሂደት ከተሰሙት መዝሙሮች እና መፈክሮች ውስጥም የሚከተሉት ይገኙበታል፡-

- "እንዴት ይረሳል? እንዴት ይረሳል? ረሳሽው ወይ፣ 97ን?"
- "ኢትዮጵያችን ሃብታም፤ እኛ ኪሳችን ባዶ፤ ቤታችን ባዶ። ባለስልጣን ሃብታም፤ በሙስና፣ በሌብነት፣ በዘረፋ…"
- "ተከብረሽ የኖርሽው ባባቶቻችን ደም፣ ባባቶቻችን ደም፤ እናት ኢትዮጵያ የደፈረሽ ይውደም፤ ወያኔ ይውደም።"
- "የመለስ ስልጣን ገደብ ይኑረው"
- "በመሳለጫ፣ በቤተመንግስት እንዳትንጫጫ"
- "ታላቁ ሩጫ፣ የኢትዮጵያ ህዝብ ብሶት መግለጫ" እና የመሳሰሉት።

ከዚህም በተጨማሪ፥ ወጣቶቹ የቅንጅትን የሁለት ጣት እና የመድረክን የአምስት ጣት ምልክቶች ሲያሳዩ ተስተውለዋል። በአንድ ወቅትም ጣቶቻቸውን ወደ አራት ኪሎ እየጠቆሙ፣ "ያዝ ያዝ ያዝ" እያሉ ዘምረዋል። ዘረኛው አምባገነን የህዝብ ድጋፍ እንደሌለው ስለሚያውቅ ዜጎች አመለካከቶቻቸውን ሊገልጹ የሚችሉባቸውን መንገዶች ሁሉ ማፈኑ ይታወቃል።

## በኢትዮጵያ ውስጥ የሚፈጸሙ የሰቆቃ ድርጊቶች . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

በዚህ አኳኋንም፥ ኢትዮጵያ ውስጥ በፖሊስ፣ በእስር ቤት ሰራተኞች እና በደህንነት አካላት የሚፈጸሙ በርካታ የሰቆቃ ድርጊቶች እንዳሉ እና፤ በተለይም በተቃዋሚ ፓርቲ አባላት፣ በተማሪዎች እና በሽብርተኝነት እና የትጥቅ ቡድኖችን በመደገፍ በሚጠረጠሩ ላይ እንደሚደርሱ መረጃዎች እንደደረሱት ጠቅሷል። በፖሊስ ጣቢያዎች እና እስር ቤቶችም ውስጥ ዜጎችን አስገድዶ ለማናዘዝ ሰቆቃን መጠቀም የተለመደ መሆኑን የሚያሳዩ በርካታ መረጃዎች እንዳሉ ገልጿል።

ከዚህ በተጨማሪም፥ እነዚህን ወንጀሎች በሚፈጽሙት የአገዛዙ ቅጥረኞች ዘንድ ተጠያቂነት እንደሌለ እና ድርጊቱን በማናለብኝነት እንደሚያካሄዱ፤ እንዲሁም ለእስረኞች በቂ ጥበቃ እንደማይደረግ ዘርዝሯል። ገለልተኛ አካላት እስር ቤቶችን ለመጎብኘት አለመቻላቸውንም መስክሯል። ከሰቆቃ ሌላም፥ በአገሪቱ ዙሪያ ህገ-ወጥ ግድያዎች፣ አፈናዎች፣ እና ህገ-ወጥ እስሮች መካሄዳቸው፤ እንዲሁም የአገዛዙ ጦር በሶማሌ ክልል ሴቶች ላይ የአስገድዶ መድፈርን ወንጀል መፈጸሙ ክፉኛ እንዳሰጋው ገልጿል።

## የቂርቆስ ክፍለከተማ ከ150 በላይ የሚሆኑ . . . (ከገጽ 2 የዞረ)

ብዙዎች መስተዳድሩ እየወሰደው ያለውን እርምጃ ቢደግፉም፣ ጥቃቱ በእወነተኛ ባለሀብቶች ላይ የተሰነዘረ እንጅ ከመንግስት ጋር በሞሞዳሞድ ያለአግባብ በከበሩትና በመንገስት ባለስልጣናት ላይ አለመሆኑንም ጋዜጣው ገልጸዋል።

የወያኔ መከላከያ ከፍተኛ መኮንኖችና ሚኒሰትሮች በቦሌ መድሀኒአለም አካባቢ እጅግ ዘመናዊ የሆኑ ቤቶችን ከህዝብ በዘረፉት ሃብትና ንብረት መገንባታቸው ይታወቃል።


**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ**
**የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**
**በ 7140፣ 7175፣ 7185 KHZ በ 41 ሜትር ባንድ እና በ 6100 KHZ በ 49 ሜትር ባንድ**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ፣ ሐሙስ እና ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት እስከ 3፡30፤ እንዲሁም ከምሽቱ 2 ሰዓት እስከ 2፡30 የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቄያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።



**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org